የብዙ ጥበብ ባለቤት የሆኑ ምሁራን አስተዋጽኦ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጐልቶ ስለማይወጣና ለአብዛኛው ሕዝብ በቀላሉ ስለማይከሰት ጠቀሜታቸውን ለመረዳት ጊዜ ይወስዳል። ይህን ሁኔታ በጉልህ የተገነዘብኩት በተለይ የዶክተር ሥርግውን ዜና ዕረፍት ከሰማሁበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

የዛሬ ሰላሣ ሦስት ዓመት ገደማ እኔና ሌሎች እንደኔ በድሮው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የታሪክ ተማሪዎች የነበርነው፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያን ታሪክ ለመማር ከዶክተር ሥርግው ክፍል ስንገባ ምን ያህል ዕድለኞች እንደነበርን በወቅቱ የተገነዘብነው አይመስለኝም። ያን የሩቅ ዘመን ታሪክ ጊዜውን ወስዶ፣ አስፈላጊውን ቋንቋ ተምሮ፣ ራሱን በሙያው ብቁ አድርጐ በቀረበ ኢትዮጵያዊ ሊቀ መምር ታላቅ ዕድል ነው። እርግጥ እኛ ያን ጊዜ ልባችን በወቅቱ ብሶት ላይ ብቻ ስላተኰረ ለለ አብዮት ከማሰብ አልፈን ዶክተር ሥርግው የተካኑበትን ሞያ በቅጡ ለማጤን ጊዜውም ዝንባሌውም አልነበረንም። የኛ ትኩረት ከለውጡ ላይ እንጂ ከጥንታዊ ታሪካችን ላይ አልነበረም።

ታዲያ ይህን ችኰላችንና መሠረት ያልጨበጥን መሆናችንን የተገነዘቡት መምህራችን ዶክተር ሥርግው “እናንተ የዛሬ ልጆች ጐጆ እንኳን ሳትቀልሱ ቤተ መንግስት ለማፍረስ ትነሳላችሁ” ይሉ ነበር። አሁን መለስ ብለን ስናስታውሰው የአባባሉን አግባብነት እንረዳለን።

በዶክተር ሥርግው ሞት የተጐዱት ቤተሰባቸውና የቅርብ ወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ለኢትዮጵያ ታሪክ ያበረከቱትን አገልግሎት የሚረዳው ወገን ሁሉ ነው።

ሹመት ሲሻኝ
ተባባሪ ፕሮፌሰርና ሊቀመንበር
ታሪክ ክፍል
ክሪስቶፈር-ኒውፖርት ዩኒቨርስቲ